6

አፍሪካ ቲቪ

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

- የአል ከውሰር ምዕራፍ

(የበጎ ነገሮች ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡ የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (3) ናቸው፡፡

- **ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

አላህ በመልዕክተኛው (ሰላላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ላይ የዋለውን ውለታና እሳቸውን የሚጠላ ሰው መንገዶቹ ሁሉ የተቆረጡ ስለመሆኑ የሚያብራራ ምዕራፍ ነው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ምዕራፉ የወረደበት ምክንያት ዐብዱላህ የተባለው የነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ልጅ በሞተ ጊዜ አንድ ዓስ ኢብኑ ዋኢል የተባለ ከሃዲ የሙሐመድ ዘር ተቆርጧል እሱ እኮ ዘር የሌለው ሲሞት አስተምህሮቱ የሚገታ ነው በማለቱ ነው ይህ ዕራፍ የወረደው፡፡

- ከውሰር ብዙ ነገሮችን ለማለት ነው የሚሉ ምሁራን እንዳሉ ሁሉ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላለፉት ነብዩ صلى الله عليه وسلم ወደ ሰማይ አርገው ከተመለሱ በኋላ እንዲህ ብለዋል፡-‹‹ጀነት ውስጥ ወደ አንድ ዳርቻዎቹ በሉል ወደ ተጌጡ ወንዝ መጣሁና ጅብሪልን ይህ ምንድ ነው? አልኩት፡፡ እሱም ይህ ከውሰር ነው አለኝ›› ያሉት የጀነት ዉሃ (ሀውድ) ነው የሚሉም ምሁራን አሉ፡፡ የሚመረጠው ግን ብዙ የሚለው ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

# በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

(1) (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ በጣም ብዙ በጎ ነገሮችን ሰጠንህ (ለገስንህ)፡፡

ከለገስንህም አንዱ ጀነት ውስጥ የሚገኘው የከውሠር ምንጭ ይገኝበታል።

(2) ለእዚህም ፀጋ አጋሪያን ለጣዖቶቻቸው መቃረቢያ ከሚያርዱት በተቃራኒ ለጌታህ ብቻ በመስገድና በማረድ ምስጋናን ለአላህ ፈጽም።

(3) ያ አንተን የሚጠላህ ሰው ነው የተረሳው እና ከመልካም ነገር ሁሉ የተቋረጠው። ስሙም ቢነሳ እንኳ በክፉ የሚነሳው እርሱ  ነው።

6

አፍሪካ አካዳሚ

## ከምዕራፉ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- 1. አላህ ለመልዕክተኛው ሙሐመድ صلى الله عليه وسلم የሰጠው ማዕረግና ክብር፤
- 2. በአምልኮ በተለይም በሰላትና በእርድ ዙሪያ ለአላህ ሊኖረው የሚገባ ፍፁምነት፤
- 3. በግፈኞች ላይ ዱዓ ማድረግ ተገቢ መሆኑን፤
- 4. ነብዩን صلى الله عليه وسلم መጥላት ለከፋ ችግር እንደሚያጋልጥ ሁሉ እሳቸውን መውደድም ለመልካም እድል እንደሚያበቃ፤

6

አፍሪካ አካዳሚ

- **ከምዕራፉ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**
- 5. ዱዓቶችን የሚጠሉና በመጥፎ የሚያስቡ ሁሉ መጨረሻቸው እንደማያምር፤
- 6. ነብዩን صلى الله عليه وسلم የጠላ ሁሉ ቆራጣ መሆኑን እንማራለን፡፡
- 7. ነቢዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) አላህ ዘንድ ያላቸው ክብር እና በቅርቢቱም ዓለም ሆነ በመጨረሻው ዓለም ጥበቃ እንደሚያደርግላቸውና ክብርን የሚለግሳቸው መሆኑን።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com